# ስለ ኢህአዴግ ህገ መንግሥት ስታሊናዊነትና አደገኛነት

ባለፈው ዲሰምበር ወር በሃገራችን የተወከሉ 18 የምእራብ ሊበራል ዲሞክራሲ መንግሥታት ተወካዮች እንደገና የኢህአዴግ ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ ነው፣ ሁለተኛ በዚህ ህገ መንግስት አማካኝነት በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ዘር ተዘርቷል:: ስለሆነም ተቃዋሚ ኃይሎች በዚህ ህገ መንግሥት ሥር በሚደረገው ምርጫ እንዲሳተፉ ጥሪ አርገዋል::

በኔ ግምት ይህ ህገ መንግሥት እንደገና ስታሊናዊ እንጂ በነዚህ በፈራሚያቹ አገሮች ካሉት ዲሞክራሲያዊ ህገመንግሥታት ጋር ግንኙነት የለውም:: ሁለተኛ በሱ አማካኝነት በሃገራችን ለሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ለውጥ በሩ የተዘጋ በመሆኑ የተዘራው ዘር የዲሞክራሲ ሳይሆን የባሰ ትርምስና ብጥብጥ ዘር ነው::

## እንደገና ስታሊናዊ ህገ መንግሥት ነው

በህገ መንግሥት ባለሙያዎች አካባቢ ስታሊናዊ ህገ መንግሥት ቲዎሪና አሰራር እየተባለ የሚታወቀው የሊበራል ዲሞክራሲ የህገመንግሥት ቲዎሪን ዋና ዋና ጽንሰ ሃሳቦች እየተቃረነ ከዲሴምበር 1936 ዓ.ም. የሶቭየት ህብረት የስታሊን ህገ መንግሥት ጋር ተጸንሶ ከዚያ ወዲህ እየዳበረ የመጣውን ቲዎሪና አሰራር ነው:: ይህ የኢህአዴግ ህገ መንግሥት እንደተሳገቱ የደርግ ህገ መንግሥት ስታሊናዊ ነው የምለው ዋና ዋና ምክንያቶች፣

1ኛ/ በአነዳደፉና በአጸዳደቁ ሂደት ከህገ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ጋር አብሮ የተወለደውን የህዝቡን ህገ መንግሥት አውጭነትና ባለሙሉ ስልጣንነት ከደ ከህዝብ ውጭ ስልጣን ላይ ባለው መንግሥት የተነደፈና የረቀቀ የጸደቀ መሆኑ

2ኛ/ የዲሞክራሲያዊ ህገመንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ጋር አብሮ የተወለደውንና የሱ ምልክትና መሰረት የሆነውን "የስልጣን ክፍፍል" ቲዎሪ ወደ ጎን በመተው በሶቭየት ህገመንግሥት ባለሙያዎች እየዳበረ የመጣውን "የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት" የሚለውን ቲዎሪ ከሥራ ላይ በማዋል በየትም ሊበራል ዲሞክራሲ ህገ መንግሥት የሌለ በሶሺሊዝም ስም በያለበት የተተከሉ መንግሥታት በሙሉ የተቀበሉት "የመንግሥት ስልጣን ከፍተኛ አካል" የሚል አንቀጽ መኖሩ

3ኛ/ እንደዚሁ ከተጻፉ ህገ መንግሥታት ቲዎሪ ጋር አብሮ የተወለደውንና እሱም ከሌለ ህገ መንግሥት ብሎ ነገር የለም እስከመባል የተደረሰለትን በነጻነት ህገመንግሥታዊ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል አለመኖሩና ከሱ ይልቅ በስታሊናዊ ህገ መንግሥት ቲዎሪ መሠረት በፓለቲካ መሰረት ለተወሰነ ጊዜ ለተመረጠ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በህግ አውጭው ቁጥጥር ስር ላለ የፖለቲካ አካል መስጠቱ

4ኛ/ የስታሊናዊ ህገ መንግሥት ቲዎሪ መሠረት ለዚህ ሳይገነስ በተደረገው "አስተዋጽአ" መሠረት ህገ መንግሥቱ እንደሌሎቹ የሊበራል ዲሞክራሲ ህገ መንግሥታት የዜጎችን መብትና የፖለቲካ ስልጣንን አወቃቀርና ቁጥጥር፣ ገደብና ክፍፍል ከመደንገግ አልፍ· የሶቭየት ህገ መንግሥት ባለሙያዎች "ፕሮግራማቲክ ፖዚቲቪዝም" በሚሉት መሠረት የአንድን ኃይል የፖለቲካ ፕሮግራም የሚያንጸባርቅ መሆኑ

ሁለተኛ ይህ ህገ መንግሥት ለዲሞክራሲና ለሰላማዊ ሂደት አደገኛ ነው:: ይህንን ለማለት የሚያበቁት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች፣

1ኛ/ በዝርዝር ታወቁ የተባሉት መብቶች እንደ አጼ ኃይለስላሴና ደርግ ዘመን ለመከበር አለመከበራቸው ምንም ዋስትና የላቸውም፣ ሲጣሱ አቤት የሚባለው ነጻ አካል ጋ ሳይሆን የዚሁ መብት የጣሰው መንግሥት አካል ጋር ነው

2ኛ/ በተጭበረበረ ምርጫ ባልሆነ የምርጫ ሥርዓት አንድ አጅግ አናሳ የሆነ ኃይል የተከለውን ህገ መንግሥት ነገ ተቃዋሚዎች አጅግ አይለው አጅግ ከፍተኛ ድምጽ አግኝተው ስልጣን ቢይዙ እንኳን ህገ መንግሥቱን እንኳን ኢህአዴግ ቀርቶ ሌላ ከሱ ያነሰ ኃይል ህገ መንግሥቱ እንዳይሻሻል በር ሊዘጋ ይችላል::

3ኛ/ምሥቲ ፖር ቲዘምን ትርጉም የሚያሳጣ ህገ መንግሥት ነው:: ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እንኳን 51 ከመቶ ቀርቶ ከዚያም በላይ የተትረፈረፈ ማጆሪቲ ቢያመጡ እንኳን ከሥራ ላይ ለማዋል የሚገደዱት የራሳቸውን ፕሮግራም ሳይሆን በህገ መንግሥት ስም በቀላሉ እንደማይሻሻል ሆኖ የቀረበውን የኢሀአዴግን ፕሮግራም ነው:: ምርጫ አሸንፎ የት ለመድረስ? የሚለው ጥያቄ አለ ማለት ነው::

እንግዲህ እነዚህን ነጥቦች ተንተን ዘርዘር አርገን እንመልከታቸው::

<u>ክፍል አንድ፣ ስታሊናዊ ህገ መንግሥት</u>

1ኛ/ <u>ህዝብ ለገዢዎች የሚሰጠው ወይስ ገዥዎች በህዝብ ላይ የሚጭኑት ሰነድ?</u>

የተጻፈ ህገ መንግሥት ሃሳብ በ18ኛው ክፍለዘመን መጨረሻ ላይ በአሜሪካና በፈረንሳይ አብዮቶች ሲጠነሰስ እንደዋና ዓላማ የተወሰዱት ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው:: አንደኛ ዋስትና ባለው ሁኔታ የህዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማረጋገጥ ሁለተኛ የገዥዎችን ስልጣን ለማዋቀርና ለመገደብ:: ሁለቱ ዓላማዎች በርግጥ የተያያዙ ናቸው:: ሆኖም የመጀመሪያዎቹ ህገ መንግሥታትና ከዚያም በ19ኛው ክፍለዘመን የተነደፉት ህገ መንግሥታት ከህዝቦች የነጻነትና የመብት ትግል ጋር እየተያያዙ ስለነበረ ዋና ዓላማቸው የገዥዎችን ስልጣን ለመገደብ፣ እነሱም እንደማንም ዜጋ በህግ እንዲተዳደሩ ለማድረግ ነበር ማለት ይቻላል:: እንደዚህም በመሆኑ በነዚህ ዘመናት ህገ መንግሥት የሚታየው "ባለሙሉ ስልጣን" የሆኑት ህዝቦች ለገዥዎች እንደሚሰጡት የበላይ መተዳደሪያ ደንብ እንጂ በምንም ዓይነት ገዥዎች ለተገዥዎች እንደሚለግሱት ሰነድ አልነበረም::

ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት ከተጻፈ ህገ መንግሥት ሃሳብ ጋር አብሮ የተወለደ ጽንሰ ሃሳብ አለ:: ይኸውም በጊዜው የፈረንሳይ አብዮታውያን በቲዎሪ መልኩ ያዳበሩት [redacted] "ፑቧር ኩንስቲትዋንት" ወይም ህዝቡ ህገ መንግሥትን ለማፍለቅ ያለው ባለሙሉ ስልጣንነት የሚለው ቲዎሪ ሲሆን ከሱው ጋር ተያይዞ የኩንስቲትዋንት አሴምብሊ ወይም የህገ መንግሥት ጉባኤ የሚለው አሠራር መጣ::

በዚህ አሠራር መሠረት ህገ መንግሥት ለዚሁ ብቻ በተመረጠ ባለሙሉ ስልጣን በሆነ አካል ይጸድቃል:: ሰነዱ ከህጎች ሁሉ በላይ በመሆኑ ገዥዎች በሌሎች ህጎች ወይም በተግባር እንዳይጥሱት በመንግሥት አካላት የሚወሰዱ ርምጃዎችም ሆኑ ውሳኔዎች ከህገ መንግሥቱ መጣጣም አለመጣጣማቸውን የሚቆጣጠር /ጁዲሻል ሪቪው የሚያካሂድ/ ነጻ አካል አለ:: ህገ መንግሥቱ እንደ ተራ ህግ ስላልጸደቀ እንደ ተራ ህግ አይሻርም ወይም አይሻሻልም:: እንደሁኔታው የተጠናከረ አብላጭነት፣ ወይም በውሳኔ ህዝብ ወይም በሁለቱ ዘዴዎች ብቻ ይሻራል ወይም ይሻሻላል::

የሶቭየት ህገ መንግሥት ቲዎሪ እርግጥ የህዝብ የበላይነት ቢልም ፑቧር ኩንስቲትዋንት በሚለው ቲዎሪ አያምንም:: ሰርቶበትም አያውቅ:: የመንግሥት ስልጣን በሆነ ዘዴ የያዘው ኃይል የህዝቡን ባለሙሉ ሥልጣን ህገ መንግሥት አውጭነት መብት ከህዝብ በህዝብ ስም ተረክቦ ህገ መንግሥት ያወጣል:: ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ በዚህ ቲዎሪ መሠረት የተተከሉትን "ህዝባዊ ዲሞክራሲያች" እንደዚሁም ትላንት የደርግን ዛሬ ደግሞ የኢሀአዴግን "የህገመንግሥት ሂደት" ብንመለከት ይህንን አሠራር ተከትለው የተተከሉ ህገመንግሥታት ሆነው እናገኛቸዋለን::

መጀመሪያ ህገ መንግሥቱ በስልጣን ላይ ባለው መንግሥት ወይም ድርጅት "የህብረተሰቡን የተለያዩ ክፍሎች በሚያካትት ሁኔታ" በተሰየመ ኮሚሽን ይዘጋጃል፣

ሁለተኛ ይህ ሰነድ ለህዝብ ውይይት ቀርቦ ተብሎ ህዝቡ ሃሳብና ማሻሻያዎችን

እንዲያቀር ይጋበዛል

ስስተኛ እነዚህ ሃሳቦች፣ ጥያቄዎች፣ ማሻሻያዎች ተለቀመው በስልጣን ላይ ካለው መንግሥት በስተቀር ለማንም ተጠሪነት ወደሌለው ግን ደግሞ የፈለገውን የህዝብ ሃሳብ ለመቀበል፣ ያልፈለገውን ለመተው ባጭሩ በህዝብ ፈንታ በህገመንግሥት ጉዳይ ራሱን ባለሙሉ ስልጣን ወዳደረገው ኮሚሽን ይላካሉ

አራተኛ ይህ ባለሙሉ ሥልጣን ኮሚሽን "ከህዝብ ተገኙ" የተባሉትን አስተሳሰቦች መለስ ዜናዊ እንዳለው "አከተተ" የመጨረሻውን ረቂቅ ያዘጋጃል:: ይህንን ረቂቅ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ወይም ድርጅት ለመጨረሻ ጊዜ አይቶ ያጸድቀዋል

አምስተኛ ይህ ያለቀለት ሰነድ እንደሁኔታው ወይ ለውሳኔ ህዝብ ይቀርባል ወይ በአንድ የመንግሥት አካል በቀጥታ ይጸድቃል::

የቀድሞዋ ምስራቅ ጀርመን የ1968 ዓ.ም ህገመንግሥት የረቀቀበትና የጸደቀበትን ሂደት እንደምሳሌ ብንወስድ ከሂደቱ መጠናቀቅ በኋላ የቀረበው ሪፖርት እንዲህ ይሏል፣ ህገ መንግሥቱ በፓርቲው በተሰየመ ኮሚሽን ከረቀቀ በኋላ

"11 ሚልዮን ዜጎች የተካፈሉባቸው 750 ሺ ስብሰባዎች ተካሄዱ:: ከነዚህ ስብሰባዎች 12384 ማሻሻያዎች ቀረቡ:: ከነዚህ ውስጥ ለህዝብ ሪፈራንደም የቀረበው ሰነድ 18 ማሻሻያዎችን ተቀብሏል:: ህገ መንግሥቱን ህዝቡ በ94.94 ከመቶ አጽድቆታል::"

ደርግና ኢህአዴግ ከዚህ ብዙም የተለዩ አይሉም:: የተከተሉት ሂደት ይህንኑ ስታሊናዊ ሂደት ነው:: ሁለቱም በተጨባጭ የህዝቡን /ማለትም በሃቀኛ ምርጫ ለህገመንግሥት አውጭነት ሊወከል የሚገባውን የህገመንግሥት አውጭነት ሙሉ መብት ረግጠው ራሳቸው በሰየሙት ኮሚሽን ህገ መንግሥት አስረቀቀዋል:: ህዝቡ በዚህ ሂደት ስላደረገው ፍሬ ቢስ ተሳትፎ ሲያትቱ፣

ደርግ በ25 ሽ ስብሰባዎች አማካኝነት 11 668 020 ህዝብ ተወያይቶ ከአምስት መቶ ሺ በላይ ጥያቄዎች፣ አስተያየቶችና ልዩ ልዩ ሃሳቦች ቀርበው በነሱ መሰረት የመጨረሻው ረቂቅ ተነድፎ ለውሳኔ ህዝብ ቀርቦ በ81 ከመቶ ጸደቀ ብሎናል::

ኢህአዴግስ? መለስ ዜናዊ አምና መጋቢት 28 ቀን ባደረገው ንግግር እንደዚሁ ስለህዝብ ተሳትፎ ቁጥር ሲደረድር ከ16 ሚልዮን ህዝብ በላይ ተሳታፊ በሆነባቸው በሰፋፊና ዲሞክራሲያዊ ውይይቶች አማካኝነት "የህገ መንግሥት ሃሳቦች ምን መሆን እንዳለባቸው"አስተያየቶች ቀርበዋል" ብሎ ነበር::

መለስ ዜናዊ ስለዚህ የህዝብ ተሳትፎ "ፍሬያማነት" ሲያስረዳ በዚሁ ንግግሩ ላይ የመጨረሻው ረቂቅ የሚሰናዳው "የህዝቡን አስተያየቶችና የህገ መንግሥት ኮሚሽኑን ጥናቶች በሚያካትት ሁኔታ ይሆናል::"ብሏል:: ደርግ የመጨረሻውን ረቂቅ በጥር ወር 1979 ዓ.ም. "ከህዝብ ውይይት በተገኘው አስተሳሰብ መሠረት የዳበረ::"ብሎ እንዳሞካሸው መሆኑ ነው::

ባጭሩ በዚህ ሂደት ደርግም ሆነ ኢህአዴግ በሃገራችን ላይ የጫኑቸው ሰነዶች የህዝቡን የህገመንግሥት አፍላቂነት ባለሙሉ ስልጣን መብት ሸረው የተቀረጹ ሰነዶች ናቸው:: ህዝብ መብቱን ለማስከበር፣ እሱ የበላይ ሆኖ ሥልጣንን ቆጥቦ፣ አከፋፍሎና ገድቦ ገዦቻችን ከህግ በታች ያረገበት ሰነድ አይደለም::

## 2. የመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል ወይስ የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት?

## 2. የስልጣን ክፍፍል ወይስ "የመንግሥት ሥ . . አንድ ወጥነት"

የተ

የተጻፈ ህገ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ሲፈጠር ጀምሮ አብሮ ያለ አስተሳሰብ የመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል ወይም ሴፓሬሽን ኦፍ ፖወር የሚለው የመንግሥት ስልጣን አወቃቀር ዘይቤ ነው:: በዚህ ቲወሪ መሠረት የመንግሥት ሥልጣን ለአንድ ለተወሰነ አካል ብቻ ተጠቅልሉ አይሰጥም:: ስልጣን አገዱም /ሆሪዘንታሊ/ ለተለያዩ የሥልጣንና የሥራ ዘርፎች ይከፋፈላል:: እነዚህም ህግ አውጭ፣ ሥራ አስፈጻሚና ፍርድ ሰጭ የሥልጣን ዘርፎች ናቸው:: እርግጥ እንደታሪካዊ ወቅቱ፣ እንደአንድ አገር ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ወይም እንደየዘርፉ መሪዎች ፐርሰናሊቲ አንዴ አንዱ ዘርፍ ሌላ ጊዜ ሌላው ዘርፍ በጊዜያዊነት ሊያይሉ ይችላሉ:: እርግጥ ይህ የስልጣን ክፍፍል ጥርት ያለ መስክ ላይ ኖረው ይችላል:: ለምሳሌ በ19ኛው ክፍለዘመን የታወቀው የአሜሪካ የከፍተኛ ፍርድቤት ዳኛ ማርሻል ለረዥም ጊዜ ባደረገው ጥረት መሰካት የተነሳ የአሜሪካንን መንግሥት የዳኞች መንግሥት እስከማለት የነበረ አሉ:: ክፍፍሉን በመመለከት በአሜሪካ ህገ መንግሥት መሠረት ሰስቱ ዘርፎች "ሳይደራረሱ" ራሳቸውን ቻለው ስለሚሠሩ የአሜሪካ ፕሬዜዳንሻል ሲስተም አንዳንዴ "ሪዥም ኦፍ ሴፓሬሽን ኦፍ ፖወር" ተብሉ ሲታወቅ ከዚሁ የሥልጣን ክፍፍል መሠረታዊ ሀሳብ ሳይወጡ "የስልጣኖች ተብብር" የሚል ሥርዓት የሚከተሉ አሉ:: በፓርላሜንታዊ ሥርዓት ህግ አውጭው ክፍል ሥራ አስፈጻሚውን ክፍል ሊገለብጥ ሲችል ሥራ አስፈጻሚው ደግሞ ፓርላሜንቱን በትና ሌላ ምርጫ የማካሄድ ሥልጣን አለው ብቻ እዚህ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ የሥልጣን ክፍፍል መሠረታዊ ሃሳብ ምን እንደሆነ ለማሳየት የፌደራል ጀርመንን ህገ መንግሥት ብጠቅስ እንደሚከተለው ይላል

"ህግ አውጭው ክፍል ለህገ መንግሥቱ ተገዠ ነው:: ሥራ አስፈጻሚውና ፍርድ ሰጭው ክፍል ደግሞ ለህግ ተገዠያች ናቸው::"

በዚህም የተነሳ የስልጣን ክፍፍል በሚሰራባቸው አገሮች በሙሉ "ከፍተኛ የመንግሥት ስልጣን ይይዛል" የሚባል አካል የለም:: ለምሳሌ በአሜሪካ ማነው ከፍተኛ ስልጣን የያዘ አካል:: ፕሬዜዳንቱ? ኮንግረሱ? ከፍተኛው ፍርድ ቤት?

ስታሊናዊ የህገመንግሥት ቲወሪ ግን እንዲያውም ዋና መለያው ከሚባሉት ነገሮች አንዱ በሥልጣን አወቃቀር ውስጥ "የመንግሥት ሥልጣን የበላይ ወይም ከፍተኛ አካል" የሚባል ነገር አለ:: ትላንት ደርግ ዛሬ ኢህአዴግ እንደዚህ ናቸው::

የሶቪየት ህገ መንግሥት ቲወሪ ገና ሲነሳ የስልጣን ክፍፍል የሚለውን ሃሳብ 'የከበርቴ አስመሳይነት' ብሉ ያስናብተዋል:: ስልጣን ስስት ቦታ የተከፈለ በመስልም ያው ተጠቅልሉ የሚያዘው በከበርቴው መደብ ነው ይላል:: ከዚህ ይልቅ ስታሊናዊው የህገ መንግሥት ቲወሪ "የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት"/ በእንግሊዝና ኢግዛክት ተርሙን አላውቀውም በፈረንሳይና ዩኒቴ ዱ ፑቧር ዔታ የሚሉት ነው/ የሚል ቲወሪ አለው:: በተጨባጭ እንደታየው የዚህ ጽንሰ ሃሳብ አደገኛነት እስከዚህም ቲወሪው ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ በሥራ ላይ ሲውል የሚያስከትለው መዘዝ ነው::

የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት ቲወሪ ከ1936 ዓ.ም. የስታሊን ህገ መንግሥት በኋላ ከተፈጠሩት ህዝባዊ ዴሞክራሲያች አንስቶ በደርግ አልፎ እስከኢህአዴግ የሚሠራበት የህገ መንግሥት ቲወሪ ነው::/ምናልባት ከ1963 ዓ.ም የቀደሞዋ የጉዝላቪያ ህገ መንግሥት በስተቀር::/

በዚህ መሠረት እነዚህ ሁሉ አገሮች "ሊከፋፈል የማይችለውን የመንግሥት ሥልጣን" ለአንድ የሥልጣን አካል ያስረክባሉ:: የዚህ ከፍተኛ ስልጣን ባለቤት ባለ ሙሉሥልጣን በሆነው ህዝብ ተመርጠ የመጣው ሸንጎ ወይም ፓርላሜንት ነው::

ሁሉም ሀገ መንግሥታት የሥልጣን ባለቤት ህዝቡ መሆኑን ያምናሉ:: ወይም ይለፍፋሉ:: ከዚህም ወዲያው አከታትለው ህዝቡ ይህንን ባለሙሉ ሥልጣን ባለቤትነት ተግባራዊ የሚያደርገው በዲሞክራሲያዊ ዘዴ በመረጣቸው ተወካዮቹ መሆኑን ይናገራሉ::

የሶቭየት ህብረት የ1977 ሀገ መንግሥት አንቀጽ 2 "በሶቭየት ህብረት የሥልጣን ባለቤት ህዝቡ ነው:: ህዝብ ይህንን ስልጣን ተግባራዊ የሚያደርገው የመንግሥት ሥልጣን የሚጨብጠው በህዝብ ተወካዮች ሶቭየቶች አማካኝነት ነው::"

ደርግ በበኩሉ በሀገመንግሥቱ አንቀጽ 3 የህዝቡን ባለሙሉ ሥልጣንነት ካረጋገጠ በኋላ "ሠርቶ አደሩ ህዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በምርጫ በሚያቋቁማቸው ብሄራዊ ሸንጎና የአካባቢ ሸንጎዎች ነው::" ይል ነበር

ኢህአዴግ እንደዚሁ በአንቀጽ 8 "የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው:: ሉአላዊነታቸው የሚገለጸው በዚህ ሀገ መንግሥት መሠረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ተሳትፎ አማካኝነት ነው::" ይለናል::

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያስፈልጋል:: እነዚህ ሀገ መንግሥታት ለምን የህዝብን ሉአላዊነት አወጁ ማለቴ አይደለም:: ይህ በሁሉ ያለ ነው:: "አስቸጋሪ" የሚሆነው ይህን ሥልጣን በህዝብ ስም የሚረከብ በመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት ቲዎሪ መሠረት አንድ አካል መኖሩ ነው:: ለምሳሌ የፌደራል ጀርመኒን ሀገ መንግሥት እንውሰድ

አንቀጽ 20 "ማንኛውም የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ከህዝብ ነው:: ህዝቡም የሥልጣን ባለቤትነቱን በምርጫና የህግ አውጭነት፣ የሥራ አስፈጻሚነትና የፍርድ ሰጭነት ሥልጣን በተጎናጸፉ ልዩ አካላት ተግባራዊ ያደርጋል::" ይላል::

በስታሊናዊ ቲዎሪ ግን ህዝቡ ሥልጣኑን የሚያስረክበው ለአንድ አካል ነው:: ይህም አካል በመረጠው ባለሙሉ ሥልጣን ህዝብ ስም የመንግሥትን ከፍተኛ ሥልጣን የሚጨብጥ አካል ነው::

የሶቭየት ህብረት ሀገ መንግሥት አንቀጽ 108 "የመንግሥት ሥልጣን ከፍተኛ አካል ሱፕሪም ሶቭየት ነው::" ይላል:: የእንዲህ አይነቱን አካል ከፍተኛነትና የሥልጣን አንድ ወጥነት በግልጽ የሚያስቀምጠው የቡልጋርያ ሀገ መንግሥት አንቀጽ 66 ይህ አካል የመንግሥትን የህግ አውጭነት፣ የሥራ አስፈጻሚነትና የቁጥጥር ተግባር ጠቅልሎ እንደሚይዝ ይናገራል::

የኛዎቹን ብንመለከት:: ደርግ በሀገመንግሥቱ አንቀጽ 62 "በኢህድሪ ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን አካል ብሄራዊ ሸንጎ ነው::" ሲል ኢህአዴግ ደግሞ በሀገ መንግሥቱ አንቀጽ 50/3/ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው::" ብሎ ደንግጓል::

የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት በዚህ መልክ ስልጣንን ለአንድ አካል ጠቅልሎ ምስጠቱ አደጋው በተጨባጭ የት ላይ ነው? በእርግጥ ይህ አካል የህዝብ ተወካይ እስከሆነ ድረስ ህግ በመሰለው ቢያወጣ፣ ይህንን ህግ ለማስፈጸም ብቃት አላቸው የሚላቸውን ሰዎች ለሥራ አስፈጻሚነት ቢመርጥ፣ ለፍርድ ሰጭነት በሙያው የሰለጠኑ ሰዎች እየመለመለ ቢያሰራ ምን አለበት?

መጀመሪያ ነገር ከታሪክ አንጻር ስናየው እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን ለህዝብ ተወካዮች ሙሉ በሙሉ ሲሰጥ ዞር ዞር ፈላጭ ቆራጭ የግለሰብ ወይም የክሊክ አመራር እንደሚያመጣ አሠራሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታየበት ኩንቨንሲዮ በመባል ከታወቀው የፈረንሳይ አብዮት ወቅት ከታየ ጊዜ ጀምሮ የተደጋገመ አደጋ ነው:: ለምን?

ዋናው ምክንያት ይህ የህዝብ ሉዓላዊነት መገለጫ የተባለው አካል ራሱ እስከዚህ

ሉዓላዊ አይደለም:: ከወዲሁ ስልጣን የያዙ ኃይሎች ለአገዛዛቸው ህገመንግሥታዊ ሽፋን ለመስጠት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው:: በመሆኑም ይህ ሥርዓት በተተከለበት ቦታ ሁሉ ይህ የበላይ አካል የተባለ ነገር ሌላ የበላይ አካል አለበት:: ነገሩን በግልጽ ያስቀመጡን የህዝባዊት ቻይናን ህገ መንግሥት አንቀጽ 16 እንመልከት

" የመንግሥት ሥልጣን ከፍተኛ አካል በቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አመራር ሥር የሚሠራው ህዝባዊ ብሄራዊ ሸንጎ ነው::"ብሎ አቀጩንና የዚህን ፓርላሜንት የበላይነት " ልክ" ይናገራል::

በተጨባጭ በያለበት ይኸው ነው:: ሚካኒዝሙ " የአሻቀብ ውክልና " የሚለው የሥልጣን "ክፍፍል" ቲወሪ ነው:: የሊበራል ዲሞክራሲ የስልጣን ክፍፍል ከሞላ ጎደል አግድምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት ቲወሪ የአሻቀብ ውክልና ወይም ቬርቲካል ዴሊጌሽን የሚለውን ይከተላል:: የስልጣን ክፍፍል አይደለም:: የሥራ ክፍፍል ነው:: ይህ አሠራር ሥልጣን በያዙት ድርጅቶች ውስጥ ከሚሠራበት የዲሞክራሲያዊ መአከላዊነት ጋር ሲተጋገዝ ቀጥታ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን ይፈለፍላል::

በአሻቀብ ውክልና መሠረት ባለሙሉ ሥልጣን ፓርላሜንት በመምረጥ ስም ሥልጣን ከባለሙሉ ሥልጣኑ ህዝብ ይነጠቃል:: ከዚህ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን አካል ደግሞ ስልጣንን የፓርቲ ወይም የድርጅት መሪዎች ይረከባሉ፣ [redacted] በዲሞክራሲያዊ መአከላዊነት ስም ጥቂት መሪዎች ይህንን ባለሙሉ ሥልጣንነት ከድርጅቱ ይረከባሉ፣ ከነዚህ ጥቂት መሪዎች ደግሞ አንድ አናሳ ቡድን ወይም አንድ ግለሰብ ሥልጣንን ጠቅልሉ ይረከባል:: በዚህ በኢህአዴግ ህገ መንግሥት አማካኝነት ወደ እንዲህ አይነቱ አደጋ እንደምናመራ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም::

በኢህአዴግ ህገ መንግሥት የፓርቲዎች ህልውና መታወቁ ይህንን ሂደት አይከለክልም:: የፓርቲዎች ህግ ይህንን መብት በሚቀልፍ ሁኔታ ሊዘጋጅና በህገ መንግሥት የታወቀውን መብት ሊሸረው ይችላል:: የፕሬስ ነጻነት ስለተባለም የፕሬስ ነጻነት እንደማይኖር ከቻርተሩ ወዲህ አይተነዋል:: የሰንሱርን አገዳ አቆምን አሉ እንጂ በተጨባጭ የሚታየው ሰንሱር ከመንግሥት ወይም ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ወደየጋዜጠኛ ቢሮ መዛወሩን ብቻ ነው:: ምንም ቁጥጥር በሌለበት ሁኔታ ታወቁ የሚባሉ መብቶች ዝርዝር መጨረሻቸው እንዲሁ ነውና:: ይህ የቁጥጥር ጉዳይ ወደ ኢህአዴግ ህገመንግሥት ስታሊናዊነት ሌላ አስፔክት ያመጣናል::

ከዚያ በፊት ግን አንድ የመጨረሻ ነጥብ ላምጣ:: የኢህአዴግ ህገ መንግሥት በዚህ የሴፓሬሽን ኦፍ ፓዎርስ ጉዳይ ነገሮችን በሶስት ክፍሎ የህግ አውጭ፣ የሥራ አስፈጻሚ፣ የዳኝነት ዘርፎች ወዘተ ስላለ የግድ የስልጣን ክፍፍልን ቲወሪ ከሥራ ላይ ማዋሉ አይደለም:: እነዚህ ዘርፎችና የስራ ክፍፍሎች በስታሊናዊ ህገመንግሥታትም ያሉ ያሠራር ዘይቤዎች ናቸው:: ግን ሁሉም ቢያንስ በቲዎሪ በባለ ሙሉ ስልጣን ሸንጎው በተጨባጭ ደግሞ በፓርቲው ወይም በድርጅቱ ቁጥጥር ስር የሚሠሩ አካላት ናቸው::

## 35/ የህገ መንግሥት ከህግ በላይነትና የቁጥጥር ጥያቄ

ህገ መንግሥት የአንድ ሃገር የበላይ ህግ ነው ማለት በተለይ በአንድ በተወሰነ ወቅት አብላጭ ኃይል አግኝቶ ስልጣን የያዘ ሥራ አስፈጻሚም ሆነ ህግ አውጭ ክፍል እንደልቡ ሊሸረውም ሆነ ከሱ ድንጋጌዎች ውጭ ሊሰራ አይችልም ማለት ነው:: ከፍ ብየ የጠቀስኩት የፌዴራል ጀርመን ህገ መንግሥት የህግ አውጭው ክፍል በህገ መንግሥቱ መሠረት

ህግ ያወጣል፣ ሥራ አስፈጻሚው ክፍል በህግ መሠረት ይሰራል.... የሚለው የህንኑ የህገ
መንግሥትን የበላይነት ያረጋግጣል::ህግ አውጭው ክፍል የሚያወጣው ህግ ከህገ መንግሥቱ
ቢጻረርስ? በሊበራል ዲሞክራሲ የህገ መንግሥት ቲዎሪ ይህ ህግ ጸረ ህገ መንግሥት ህግ
ተብሎ ይሻራል:: በስታሊናዊ ቲዎሪ ግን በመጨረሻ"በባለ ሙሉ ስልጣኑ" የጸደቀው ህግ የ
ህገ መንግሥቱን አንዱ አንቀጽ የሚጻረር ከሆነ ይኸናው እንደተሻሻለ ወይም ይበልጥ ገለ
ጽ በሆነ መልክ እንደተተረጎመ ተቆጥሮ ይሻራል:: በተጨባጭ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ግ
ልጽ ነው:: በሁለቱም አስተሳሰቦች የህገ መንግሥት የበላይነት ቢታወጅም በሊበራል ዲሞክ
ራሲ ይህ የበላይ ህግ በሌላ በተራ ህግ እንዳይጣስ፣ በሥራ አስፈጻሚው ዘርፍ ውሳኔዎችም
ሆነ ድርጊቶች "ህገ መንግሥት ወጥ" እንዳይሆኑ የሚቆጣጠር ነጻ ኃይል ወይም አካል አለ
የምእራቦች ዲሞክራሲ የህገመንግሥት ቲዎሪ ለዚህ የቁጥጥር አካል ከሚሰጠው ኢምፖርታንስ
የተነሳ አንዳንድ የህገመንግሥት ምሁራን ይህ የነጻ ቁጥጥር ሚካኒዝም እስከሌለ ድረስ ህ
ገ መንግሥት ብሎ ነገር የለም እስከማለት ይደርሳሉ::

ይህ ነጻ የቁጥጥር አካል እንደየሃገሩ የተለያዩ መልኮች ይኖሩታል:: በአሜሪካን
አገር በየደረጃው ያሉ ዳኞች በሎም ሱፕሪም ኮርቱ ይህ የቁጥጥር መብት አለው:: በሌሎች
የምእራብ አገሮች የሥራ ዋስትና የተረጋገጠላቸው ዳኞች ተሰይመው በነጻ የሚሰሩበት "የህ
ገ መንግሥት ፍርድ ቤት" አሏቸው:: /ለምሳሌ ጀርመንና ጣልያን/ ፈረንሳይ የህገ መንግሥ
ት ካውንስል የሚባል አባላቱ በማይንቀሳቀስ ሁኔታ ለዘጠኝ ዓመት የተሰየሙበት አካል ይህ
ን የቁጥጥር ተግባር ያከናውናል:: ወዘተ

ዋናው ቁም ነገር ይህንን ቁጥጥር ለማካሄድ የተመረጡ ግለሰቦች ለዚህ ቦታ የበቁ
ት /ቢያንስ በመርህ ደረጃ/ በፖለቲካ አቋማቸው ተመርጠው ሳይሆን በሙያ ብቃታቸው፣ በአስ
ተሳሰብ ብስለታቸው መመረጣቸውና የሚሰጡትም ብያኔ በፖለቲካ አቋማቸው ወይም በድርጅት አባ
ልነት ወይም ተወካይነት ያልተበከለ ውሳኔ መሆኑ ላይ ነው:: ይህንን ለማድረግ እንዲችሉም
የአቋም ነጻነታቸውን የሚያረጋግጡባቸው ሚካኒዞች ይኖራሉ:: ወይ በማይታደስ ሁኖታ ለተወ
ሰኑ ዓመታት ይሾማሉ፣ ወይ በገዛ ፈቃዳቸው ጡረታ እስኪወጡ ድረስ የማገልገል መብት አሏቸ
ው::

በስታሊናዊ ህገ መንግሥት ቲዎሪ ይህ ሰነድ ዝቁ. ብለን እንደምናየው የአንድ ሥልጣ
ን የጨበጠ ኃይል የፖለቲካ ፕሮግራም እንጂ እስከዚህም የሃገር መተዳደሪያ ደንብ ስላይደለ
እንደዚሁም ደግሞ በሥርዓቱ ውስጥ ባለሙሉ ስልጣን ተብሎ የተሰየመ አካል ስላለ ማለትም ህ
ገ መንግሥት ለዚህ ድርጅታዊ ዓላማና ለዚህ አካል ታዛዥ ስለሆነ የቁጥጥር ጥያቄ እንደዋና
ነገር አይቀጠርም:: ከፍ ብየ እንዳልኩት አዲስ መጤ የሆነ የፖርላሜንት ህግ የህገመንግሥ
ቱን አንቀጽ ከተጻረረ የሚሻረው ይኸናው ነው:: ነጻ ተቆጣጣሪ አካል የለም::

አንዳንዴ ፖርላሜንት የሚያወጣው ህግ ምንም ቁጥጥር የለበትም:: የሶቭየት ህብረት
ፌዴራል ህገጋት፣ በፖላንድ፣ በሃንጋሪ፣ በቻይና፣ በሰሜን ኮርያና በቬየትናም በመጨረሻ የ
ወጣው ህግ አንዱን የህገ መንግሥት አንቀጽ ከተጻረረ ይህ አንቀጽ እንደ "ተሻሻለ" ተቆጥሮ
አዲሱ ህግ ይጸናል::

በሌሎች አገሮች ህገ መንግሥት የሃገሪቱ የበላይ ህግ ተብሎ ቢታወቅምና አሱን የሚ
ጻረሩ ህግጋትም ሆኑ ውሳኔዎች ተፈጻሚነት የላቸውም ቢባልም /እንደ ደርግ አንቀጽ
እስከ ኢህአዴግ አንቀጽ 9/1/ አንድ ህግ ወይም ውሳኔ ከህገ መንግሥቱ ጋር መጣጣም አለ
መጣጣሙን የሚወስኑት ዝር ዝር አነሱው ናቸው:: በብዙ የቀድሞ ህዝባዊ ዲሞክራሲ አገሮች
ይህን ቁጥጥር የሚያካሄዱት ራሳቸው ፖርላሜንቶቹ ነበሩ:: አንዳንዴ በቀጥታ:: እንደ ቡል
ጋርያ፣ ሩማንያ፣:: ወይ ደግሞ ፖርላሜንቱ ራሱ ወይ በቀጥታ ወይ በተዘዋዋሪ በሚፈጥረውና
በሚቆጣጠረው ኮሚስዮን:: እንደ 1976 ዓ.ም. የአልባንያው ህገ መንግሥት:: ኢህአዴግ

"እንዳጋጣሚ" የመረጠው ከሞላ ጎደል ይህንን የአለባንያን ሲስተም ነው::

ከፍ ብየ እንዳለኩት በሰፊፋ ደረጃ ደርግም ኢህአዴግም የህገ መንግሥትን የበላይ ህግነት ይቀበላሉ:: ኢህአዴግ ከደርግ ቀዳው በሚመስል አነጋገር::

የደርግ አንቀጽ 108 "የኢህዲሪ ህገ መንግሥት የሃገሪቱ የበላይ ህግ ነው:: ማንኛውም ህግና ውሳኔ ከህገ መንግሥቱ ጋር የሚጻረር ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም::" ይላል::

ኢህአዴግ ደግሞ በአንቀጽ 9/1/ "ህገ መንግሥቱ የሃገሪቱ የበላይ ህግ ነው ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለ ሥልጣን ውሳኔ ከህገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም::"ይላል::

ታዲያ ማነው አንድ ህግ፣ ውሳኔ ወይም ርምጃ ህገ መንግሥቱን መቃረኑን አለመቃረኑን የሚበይነው:: ዝር ዝር አነሱው ናቸው:: ደርግ "በሸንጎ ውክልና" መርህ መሠረት ሸንጎው በማይሰበሰበበት ወቀት /ማለትም በዓመት 350 ቀን/ ሥልጣኑን ተረክቦ በውክልና ሙሉ ስልጣን በሚይዘው የመንግሥት ምክር ቤት አማካኝነት::/አንቀጽ 82/ማለትም እንደ ቀድሞዎቹ ቡልጋሪያና ሩሜንያ::

ኢህአዴግ ደግሞ እንደቀድሞይቱ አልቤንያ ህግ አውጭው ክፍል ራሱ በሚሰይመውና በሚቆጣጠረው የተለየ አካል አማካኝነት::

በኢህአዴግ ህገ መንግሥት ለነገሩ የህገ መንግሥት ፍርድ ቤት የሚባል ጉድ አለ እንደ ቀድሞይቱ ዩጎዝላቪያ:: እንደ ጀርመን፣ እንደጣልያን:: ግን ማመሳሰሉ በስም ብቻ ነው:: ይህ ፍርድ ቤት ከተጠቀሱት የህገ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም::

አንደኛ ነጻ አይደለም:: አስራ አንድ አባላት አሉት:: ስድስቱ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ናቸው:: ሶስቱ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት "አቅራቢነት" በፕሬዚዳው ይሾማሉ፣ ሁለቱ ማለትም የፍርድ ቤቱ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በተወካዮች ምክር ቤት የተሰየሙት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ናቸው::ህገመንግሥቱ ስለነዚህ ሰዎች የሥራ ይዘታ ዋስትና ምንም አያወራም:: በማይንቀሳቀስ ሁኔታ ለዚህ ያህል አመት ተሰይመዋል አይልም:: ምንም ዋስትና የላቸውም:: በዚህ ላይ ስድስቱ /ማለትም ማጆሪቲው/ መጀመሪያውኑ በገለልተኛነታቸው፣ ከፖለቲካው ዓለም ምንም ወገናዊነት ባለማሳየት የተመረጡ "ሽማግሌዎች" አይደሉም:: በፖለቲካ አቋማቸው ተመርጠው ለዚህ የበቁ ዜጎች ናቸው:: የህግ አውጭው ዘርፍ አባላት ናቸው:: ባጭሩ ምንም ነጻነት የሌለው እንደአለባንያ የህግ አውጭው ዘርፍ ኰሚሽን ነው ማለት ይቻላል ይህ ፍርድ ቤት ለዚያውም ደግሞ ምንም እዚህ ግባ የሚባል ሥልጣን የለውም::

ሁለተኛ ይህ ፍርድ ቤት ህገ መንግሥት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ለመፍረድ ባለሙሉ ሥልጣን ፍርድ ቤት አይደለም:: አሳዳሪያቻቸውን ለማወናበድ ሆን ብለው ይህንን ስም ሰጡት እንጂ ፍርድ ቤት ተብሎ ከተሰየመ አይቀር ፍርድ መስጠት መቻል ነበረበት::ይህ የኢህአዴግ ፍርድ ቤት ግን ያለው መብት የመፍረድ ሳይሆን "አስተያየት የመስጠት"ሥልጣን ነው:: የመወሰን ሥልጣን የለውም:: በአንቀጽ 83 መሠረት ህገ መንግሥታዊ ቁጥጥር የማድረግ መብትና ስልጣን የተሰጠው የህግ አውጭው ክፍል አካል የሆነው፣ በፖለቲካ አቋም ለተወሰነ ጊዜ ተመርጠው የመጡ፣ በጊዜው ሁኔታ ምርጫ አሸንፈው የመጡ የፖለቲካ ሰዎች አባል የሆኑበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው:: ይህ የፖለቲካ ቁጥጥር እንጂ ገለልተኛ የሆነ ህገመንግሥታዊ ቁጥጥር ሊባል አይቻልም:: በኢህአዴግ ህገ መንግሥት ይህንን ለማካሄድ የተሰየመ ነጻ አካል የለም ማለት ነው::

## 45/ ህገ መንግሥት "ህግ" ወይስ ህገ መንግሥት "ፕሮግራም"

በመሠረቱ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት የህዝቦችን መብት ዋስትና ባለው ሁኔታ ለማረጋገጥ፣ የገዢዎችን ስልጣን ገድቦ ለማደላደልና እነሱም በህግ መሠረት እንዲሰሩ ለማስገደድ የሚያገለግል ሰነድ ነው:: የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል ነክ ፖሊሲዎች ዝርዝር ካታሎግ አይደለም:: እንዲያውም አንዱ ዓላማው በነዚህ ጥያቄዎች ላይ የተለያዩ ፖሊሲዎች ያላቸው የተለያዩ ፓርቲዎች በህዝብ ፊት በምርጫ እየተወዳደሩ ካሸነፉ እንዴት አገር እንደሚያስተዳድሩ ከተሸነፉ ደግሞ እንዴት እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ መብታቸው እንደሚከበር በዝርዝር የሚደነግግ ሰነድ ነው::

አንድ ህገ መንግሥት ይህንን መድረክና ከለለ ወይም ፍሬም ወርክ ከማቅረብ አልፍ ዝርዝር የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የባህል ፖሊሲዎችን እያበራከተ በሄደ ቁጥር፣ እነዚህ ዝርዝር ፖሊሲዎች ከፓርቲ ፕሮግራምነት አልፈው ተርፈው ህገ መንግሥታዊ ፖሊሲዎች እየሆኑ በሄዱ ቁጥር የመልቲ ፓርቲዝም መድረክ እየጠበበ ይሄዳል:: በግልጽ የአንድ ፓርቲ ሥርዓት ነኝ የሚል ኃይል በነገሰበት አገር እንዲህ መሆኑ ምንም አያስገርምም:: መልቲ ፓርቲዝም ፈቅጃለሁ፣ ምርጫም ሊካሄድ ይችላል የሚል ኃይል ግን በርእዮተ ዓለማቸው ግራ፣ ቀኝ መሃል ወዘተ እያሉ ፓርቲዎች ሊወዳደሩ ይችላሉ ካሉ በኋላ ግን ህገ መንግሥቱ የአንዱን ፓርቲ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል ፖሊሲዎች ማንጸባረቅ የለበትም:: እንዲህ ካረገ ታዲያ ምርጫ ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርበታል::

ለማንኛውም የሶቪየት ስታሊናዊ ህገ መንግሥት ቲዎሪ በዚህ መስክ ያደረገው አስተዋጽኦ የሶቭየት ህገ መንግሥት ባለሙያዎች ፕሮግራማቲክ ፖዚቲቪዝም በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ይጠቃለላል:: ህገ መንግሥት በድን ሰነድ ሳይሆን ህያው የሆነ የትግል መሣሪያ ነው:: ያለን የፖለቲካ ግንኙነትና የፖለቲካውን ሥርዓት አወቃቀር ከመደንገግ አልፍ መሄድ አለበት:: የህብረተሰቡን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የሞራላዊና ባህላዊ አወቃቀር ነድፍ ማስቀመጥ አለበት:: ከዚህም አልፍ የህብረተሰቡን አስተዳደግ አቅጣጫ በቅድሚያ ቀይሶ ወደዚህ አይዲል የሚደረገውን ጉዞ ማገዝ ይኖርበታል:: ባጭሩ ስታሊናዊ ቲዎሪ ህገ መንግሥት የድርጊት ፕሮግራምም ነው::

ከዚህ የሶቭየት አስተዋጽኦ በመነሳት አንዳንድ የህገመንግሥት ባለሙያዎች እንዲያውም በዚህ መስፈርት በመጠቀም ህገ መንግሥታትን ከሁለት ታላላቅ ጎራዎች ይከፍሏቸዋል:: በአንድ በኩል ህገ መንግሥት "ህግ" አለ:: በሌላ በኩል ህገ መንግሥት "ፕሮግራም" የሚሉት በቀድሞዎቹ ህዝባዊ ዴሞክራሲዎች፣ በደርግ ዘመንና ዛሬ በኢህአዴግ ሥር ያሉት ህገ መንግሥታት ከዚህኛው ጎራ የሚደመሩ ናቸው:: እዚህ ላይ ነገሮች በይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ ሶስት ነጥቦችን ማንሳት ያስፈልጋል፣

አንደኛ/ ከምብት ጥበቃና ከመንግሥት አወቃቀር አልፈው ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚገቡት ህገ መንግሥት "ፕሮግራም" የተባሉት ብቻ አይደሉም:: ትምህርት ለሁሉም፣ ሥራ ላጡ ሥራ፣ ለድኩማን ርዳታ፣ ሳይንስ እንዲስፋፋ ማበረታታት፣ ከዚያም አልፍ ለጠቅላላው ህብረተሰብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሬትን፣ ንብረትን፣ ፋብሪካን ወዘተ ካሣ እየሰጡ በመንግሥት ቁጥጥር ስር የማድረግ ፖሊሲ በብዙ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥታት ያለ ነው:: ክፋትም የለውም:: ማንም መንግሥት ቢሆን ሥራ እንዲስፋፋ፣ ትምህርት እንዲስፋፋ ወዘተ ጥረት የማድረግ ግዴታ ህገ መንግሥታዊ ግዴታ ሊሆን ይችላል:: ለዚህ የፌዴራል ጀርመንንና የጣልያንን ህገ መንግሥታት ማየት ይበቃል::

ችግሩ እነዚህን ፖሊሲዎች ሥራ ላይ ለማዋል ምን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንከተል የሚለው ጥያቄ ላይ ነው:: ኩሌክቲቫይዝድ የሆነ ኢኮኖሚ፣ ነጻ ኢኮኖሚ ወይስ ቅይጥ ኢኮኖሚ? አንዱ ፖርቲ እነዚህን ዓላማዎች በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ከሥራ ላይ አውላለሁ ሊል ይችላል፣ ሌላው በቅይጥ ኢኮኖሚ ወዘተ ህገ መንግሥት "ፕሮግራም" ከሌሉቹ የሚለየው እነዚህን ፖሊሲዎች ከሥራ ላይ ለማዋል ፍቱንና አማራጭ የሌለው ዘዴ ዋና ዋና የኢኮኖሚ አውታሮችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማድረግ ነው ብሎ ይህንን የፖርቲ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በህገ መንግሥቱ ያሰፍረዋል:: ደርግና ኢህአዴግ የጫኑብን ህገ መንግሥታት ከዚህናው ጉራ የምንከታቸው እስከዚህም ማህበራዊ፣ ባህላዊ ፖሊሲዎች እያሉ በመደርደራቸው ሳይሆን እነዚህን ፖሊሲዎች ከሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ነው የሚሉትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ራሳቸው ከፖርቲ ፕሮግራማቸው ቆድተው ህገ መንግሥቱ ውስጥ ማስፈራቸው ነው:: 90 ከመቶ ከህዝቡ በአርሻ በሚተዳደርበት አገር የደርግ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 መሬት የመንግሥት ነው ያለውን የኢህአዴግ ህገ መንግሥት ደግሞ አንቀጽ 40/3/ ላይ ይህንኑ ፖሊሲ ቃል በቃል ሲደግመው ህገ መንግሥቱን የነሱ ወገናዊ አመለካከት ማራመጃ ፕሮግራም አርገውታል ማለት ነው::

ሁለተኛ በሶስተኛው ዓለም በዚህ መልክ የሚጸድቁ "ሁለገብ" ህገ መንግሥታት ከፕሮግራምም ፕሮግራም ናቸው:: የስታሊን ህገ መንግሥት ሥራ ለሁሉም ሲል ሥራ ለሁሉም ይሰጣል:: ጤና ለሁሉም ሲል የጤና አገልግሎትን ለሃገሩ በሙሉ ያዳርሳል:: ኢህአዴግና ደርግ በህገ መንግሥቱ የሚለፍፉቸው ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ምንም አስገዳጅነት የላቸውም:: የሃገሪቱ አቅም እስከፈቀደ ድረስ፣ ሁኔታው እንዳመቸ፣ ይእናታችን መቀነት ካላደና ቀፈን...እያሉ ነው ፖሊሲያቸውን የሚደረድሩት::

ሶስተኛ ግልጽ መሆን ያለበት ሌላ ጉዳይ አለ:: የኢህአዴግን የኢኮኖሚ ፖሊሲ መቃወምም ሆነ መደገፍ ከዚህ ትንተና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: ዛሬ በኢትዮጵያ ለምሳሌ ብዙ ኃይሎች መሬት ለገበሬው በግል ሃብትነት መሰጠት አለበት ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ይህንን የኢህአዴግ ፖሊሲ ሊደግፉ ይችላሉ:: ዋናው ጥያቄ ይህ ሳይሆን የአንድ ድርጅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለምን በህገ መንግሥት ይሰፍራል? በህገ መንግሥቱ መሬት የመንግሥት ነው ከተባለና ህገ መንግሥቱን ለማሻሻል ኢህአዴግን በ51 ከመቶ ማሸነፍ ካለበቃቸው የሌላ ፖሊሲ አራማጅ ኃይሎች መንግሥት ይዘው ምን ሊሆኑ ነው የሚለው ጥያቄ ነው ከዚህም ተያይዞ ይህ የኢህአዴግ ፕሮግራማዊ ህገ መንግሥት ምርጫንና መልቲ ፖርቲዝምን ትርጉም የለሽ አያደርጋቸውም ወይ የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው::

ይህ እንግዲህ ስለዚህ ህገ መንግሥት አደገኛነት የሚታየኝን ወደ መዘርዘር ያመጣናል::

## ክፍል ሁለት ለሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ሂደት አደገኛ ሰነድ ነው

ፈረንጆቹ በዚህ ህገ መንግሥት መሠረት በሃገራችሁ የዲሞክራሲ ዘር ተዘርቷልና ምርጫ ውስጥ ተሳተፉ ሲሉን ሁለት መሠረታዊ አለመግባባቶች ይታዩኛል:: ለመከበራቸው ምንም ዋስትና የሌላቸው ሰብአዊ መብቶች ስለተደረደሩ ብቻ በሃገራችን ዲሞክራሲ የሰፈነ መስሏቸዋል:: ወይም እያወቁ ሊያታልሉን ይፈልጋሉ:: ሁለተኛ ደግሞ የዚህ ህገ መንግሥት ከሥራ ላይ የሚውሉ አንዳንድ አንቀጾች የሰላማዊ ለውጥን በር እንደሚዘጉና ተዘረጋ የሚሉትን መልቲ ፖርቲ ሲስተም ውሃ የሚያገቡ መሆናቸውን ልብ ያሉት አይመስለም:: የኔ አስተሳሰብ ግን

1ኛ/ የታወቁት የሰው ልጅና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለመከበራቸው ምንም ዋስትና

የሏቸውም:: ተደጋግሞ እንደተባለው ዲሞክራሲ ባልሰፈነበት፣ መብቶች ባልተከበሩበት አገር እነዚህ መብቶች በህገ መንግሥት ታውቀዋል ስለተባለ ብቻ የሚከበሩበት ምንም ዓይነት ተዓምር የለም:: እንደዚህ ቢሆን ኖሮ ሃገራችን በተለይ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ የ1948 ዓ.ም. የተሻሻለ ህገ መንግሥት ወዲህ የሰው ልጅ መብት የተረጋገጠባት አገር በሆነች ነበር:: በተከታታይ የተፈራረቀብን አገዛዞች በየጊዜያቸው ከውጭ አሰባሰቦቻቸው በቀለቧቸው መፈክሮች እየተመጻደቁ እነዚህን መብቶች አውደውልናል:: አጼ ኃይለሥላሴ "በዘመኑ ስልጣኔ" ስም ደርግ "በሶሻሊዝም ግንባታ" መፈክር፣ ኢህአዴግ ደግሞ በ"መድበለ ፓርቲ ሥርዓት"ስም:: ግን ሶስቱም አገዛዞች እነሱ ከህግ በታች ሆነው የሚተዳደሩበት፣ የነዚህ መብቶች መከበር በሚመለከት አስተማማኝ ዋስትና የሚሰጡ ህገ መንግሥታት "ለገሰውን"አያውቁም:: ይህንን የዋስትና ጉዳይ በተከከለ እስካልመለሱ ድረስ ደግሞ በሰነዶቻቸው ላይ እነዚህን መብቶች እንደልብ ሊደረድሩ ይቻላሉ::

የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት እነዚህን መብቶች በ28 አንቀጾች ያረጋገጠ ህገ መንግሥት ነበር:: የኀሪስ፣ የሰላማዊ ሰልፍ፣ የመደራጀት...ያልታወቀ መብት አልነበረም:: ንጉሡ የተሻሻለውን ህገ መንግሥት ለወቅቱ ፓርላሚንት ሲያቀርቡ ሚያዝያ 23 ቀን 1948 ዓ.ም. ባደረጉት ንግግር ህገ መንግሥቱ "የሰው ልጅ መብቶችን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ከሰለጠኑት አገሮች የተወሰዱ አንቀጾች" የያዘ መሆኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ አብስረው ነበር::

ደርግ እነዚሁኑ መብቶች በ24 አንቀጾችና በ56 ንዑስ አንቀጾች ቃል ሲገባልን ኢህአዴግ በበኩሉ በ30 አንቀጾችና በ103 ንኡስ አንቀጾች ከደረደረልን በኋላ እንዲያውም ካልበቃችሁ ብሎ ዩኒቨርሳል ዲክላሬሽንን አክሎልናል::

ግን ትላንትም ዛሬም ሃገራችን የህግ በላይነት የተረጋገጠባት አገር አይደለችም:: ለምን?.

የአጼ ኃይለ ሥላሴ ህገ መንግሥት ለህዝቡ የሚያውቃቸውን መብቶች ሁሉ በህጉ መሠረት እያለ ይቀልፋቸው ነበር:: የደርግ ህገ መንግሥት በአንቀጸ 58 በሰነዱ የታወቁት መብቶች "የመንግሥትንና የህብረተሰቡን ጥቅም ለማስከበር ሲባል" ሊታገዱ እንደሚቻሉ ይደነግጋል:: ኢህአዴግ በተለያዩ አንቀጾች እነዚህ መብቶች በህጉ መሠረት እንዴት ሊታገዱ እንደሚቻሉ ይደረድራል:: ለምሳሌ አንቀጸ 26/3/ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅን የመሰለ መሰረታዊ መብት ስፍር ቁጥር በሌላቸው ብቻ ሳይሆን እንደልብ ለትርጓሜ በሚያመቹ ኩንዲሽንስ ይገድባቸዋል

"አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሄራዊ ደህንነትን፣ የህዝብን ሰላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ህጐች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይቻልም::"

ችግሩ እንደዚህ ዓይነቶቹ በህጉ መሠረት የሚሉ ገደቦች መኖራቸው አይደለም:: ችግሩ ህዝቡ በእነዚህ መብቶች ሲጠቀም በህጉ መሠረት መሆኑን አለመሆኑን፣ የህብረተሰቡን ጥቅም መጻረር አለመጻረሩን፣ የሃገር ደህንነት መናጋቱን አለመናጋቱን፣ ለህዝብ ሞራል አደገኛ ሁኔታ መፈጠሩን አለመፈጠሩን ባጭሩ እነዚህ መብቶች መገደብ አለመገደባቸውን የሚወስኑት አገዛዞቹ መሆናቸው ላይ ነው::

የሃገራችን ችግር በጠቅላላው በህብረተሰቡ ዲሞክራሲ መነፈግ ጋር ተያይዞ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ ህገ መንግሥቱን የሚተረጉምና ገዥዎቹ በህጉ መሠረት መስራት አለመስራታቸውን የሚቆጣጠር አካል አለመኖሩ ነው:: የኢህአዴግ ህገ መንግሥት እንዲህ ዓይነት ሚካኒዝም ስለሌለው በዚህ አገዛዝ ሥር መብቶች ይከበራሉ ማለት ዘበት ነው::

2ኛ/ ይህ ህገ መንግሥት በአንድ እጅግ አናሳ በሆነ ኃይል ተተክሎ በብዙሃን ወይም ደግሞ በውሳኔ ህዝብ እንደማይሻሻል ሆኖ የተጠረቀመ ሰነድ ነው:: እርግጥ ህገ መንግሥት እንደተራ ህግ በተራ ድምጽ ብልጫ አይሻሻልም:: የሚሻሻለው ወይ በፓርላሜንቱ የተጠናከረ ማጆሪቲ ወይ ደግሞ በቀጥታ በሬፈራንደም:: ፌዴራል በሆኑ አገሮች ትንሽ ለየት ሊል ይችላል:: ለምሳሌ አሜሪካ አንድን አንቀጽ ለማሻሻል የሚቻለው የኮንግረሱ አባላት 2/3ኛ ወይም የአባል መንግሥታት ኮንግረሶች 2/3ኛ ሃሳብ ሲያቀርቡና ከአባል መንግሥታት ኮንግረሶች 3/4ኛው ሲስማሙ ነው::

እና አገር ኢህአዴግ ነገሩን ቀላልፍታል:: እንደና በሬፈራንደም /ማለትም ከህዝቡ 51 ከመቶ/ ህገ መንግሥት ሊሻሻል ወይም ሊቀየር አይችልም:: በስተቀረ ሁለት ዓይነት ደረጃዎች አሉ:: ለመሻሻል እጅግ ከፍተኛ ኩንሳንሰስ የሚጠይቁ:: እነሱም የህዝብ መብቶች ተብለው በህገ መንግሥቱ የሰፈሩት / በተለይ የመገንጠል መብትን፣ የመንግሥት የመሬት ባለሃብትነትን .../ የሚመለከቱ አንቀጾችና የህገ መንግሥቱን የማሻሻል ፕሮሲጀር የሚመለከቱት አንቀጽ 93 እና 94:: እነዚህን ለመንካት ከተፈለገ፣

1ኛ/ ሁሉም የክልል ፓርላሜንቶች በድምጽ ብልጫ መስማማት አለባቸው::

2ኛ/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምጽ መስማማት አለበት

3ኛ/ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትም በ2/3ኛ ድምጽ መስማማት አለበት::

ሌሎችን የህገ መንግሥት አንቀጾች ለማሻሻል ፕሮሲጀሩ ላላ ሊል ይችላል:: ማለትም አንድ አንቀጽ የሚሻሻለው በሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ 2/3ኛ ድምጽ ሲያገኝና ከክልል ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛው በድምጽ ብልጫ ሲስማሙ ነው::

ይህ እጅግ የጠበቀ የህገ መንግሥት ማሻሻያ ፕሮሲጀር በተለይ የመጀመሪያው ሊያመጣ ስለሚችለው አደጋ ሶስት ነገሮች ማለት ይቻላል፣

1ኛ/ ይህንን ህገ መንግሥት የተከለው ኃይል በተጭበረበረ ምርጫ የመጣ ህብረተሰቡን የማይወክል እጅግ አናሳ ኃይል ነው:: የህገ መንግሥቱን ጉባኤ ለመምረጥ የተጠቀመበት የምርጫ ስርዓት እራሱ ኢህአዴግ በህዳር ወር 1986 ዓ.ም. ለህዝብ ውይይት ብሎ ባቀረበው ሰነድ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጠው ይህ የምርጫ ሥርዓት ብዙሃኑን ህዝብ የማይወክል ኃይል ወደ ሥልጣን የማምጣት አደጋ አለው ብሎ ነበር:: በምንም ዓይነት ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ማጆሪቲና ማይኖሪቲ በአንድነት ተሰብስበው የጋራ ሰነድ ለማውጣት ከፈለጉ ይህ የምርጫ ስርዓት የሚሰራ አይደለም:: እንደካምቦዲያ፣ እንደደቡብ አፍሪካ የፕሮፖርሽናል ሪፕሬዜንቴሽን የምርጫ ሥርዓት ከሥራ ላይ መዋል ነበረበት:: የሆነ ሆኖ ኢህአዴግ የተከለው የህገ መንግሥት ስም የቀረበው የፖለቲካ ፕሮግራሙ የአንድ እጅግ አናሳ ኃይል ህገ መንግሥት እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: በመሆኑም ምናልባት ነገ በአንድ ተዓምር ተሸንፌ ከሥልጣን ብወርድ ይህንን ህገ መንግሥቴን ካሁኑ ልቀላልፍ ያለ ይመስላል:: በኢህአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ ቁልፍ ቦታ የያዙት የብሄር ጥያቄና የመሬት ጥያቄ "እስከወዲያኛው" ድረስ በማይነኩበት ሁኔታ የተቀለፉት ለዚህ እንደሆነ ግልጽ ይመስለናል::

2ኛ/ ከፍ ብየ እንዳልኩት ህገ መንግሥትን ለማሻሻል ጠበቅ ያለ ፕሮሲጀር መኖሩ ብቻውን እንግዳ ነገርም አይደለም:: አደገኛም አይደለም:: አደገኛ የሚያደርገው የኢህአዴግ ህገ መንግሥት ተራ ህገመንግሥት አይደለም:: የድርጅቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮ

ፕሮግራሞች የተከታተቡት ሰነድ ነው:: ይህም ማለት በመልቲ ፓርቲ ሲስተም መሠረት ምርጫ አሸንፈው ሥልጣን የሚይዙ ኃይሎች የራሳቸውን የተመረጡበትን ፖሊሲ ከስራ ላይ ለማዋል ከፈለጉ መጀመሪያ ህገ መንግሥቱን መቀየር አለባቸው:: 25 ከመቶ ከህዝቡ መወከሉ የሚያጠራጥረው ኃይል የቀየሰውን ፖሊሲ 60 ከመቶ የህዝብ ድጋፍ አግኝቶ የመጣ ዲሞክራሲያዊ ኃይል ሊቀይረው አይችልም ማለት ነው:: ማለቂያ ወደሌለው ትርምስና እልቂት ሊያመጣ የሚችለው ነገር ዲሞክራሲ በዚህ መልክ የቆም ስቀሉን ማየቱና የሰላማዊ ለውጥ ጉዳና በዚህ መልክ ጥርቅም ብሎ መዘጋቱ ነው::

35/ ህገ መንግሥቱ የሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ ሂደትን በር የዘጋል:: የጭቅጭቅ የትርምስ፣ የደም መፋሰስ በር ይከፍታል እንጂ የዲሞክራሲን ዘር አለዘራም:: እዛው መሬት ፖሊሲ ላይ እንመለስ:: ነገ በሃገሪቱ በሙሉ ህዝቡ በ80 ከመቶ ይህ ፖሊሲ እንዲቀየር ይጠይቅ:: ይህንንም በምርጫ ይግለጽ:: በመሃከል ደረጃ ያሉት ሁለቱም ሸምብሮች ሃሳቡን በ80 ከመቶ ይደግፉ:: ከዘጠኙ ክልሎች ስምንቱ ውስጥ እንደዚሁ የተጠናከረ ማጆሪቲ መሬት የግል ሃብት ይሁን ይበል:: የአማራው ክልል፣ የኦሮምያ ክልል፣ የደቡብ ህዝቦች ክልል...ሁሉም ይስማሙ:: አንድ ክልል ብቻ ለምሳሌ በህዝብ ቁጥር አነስተኛ የሆነው የቤኒሻንጉል ክልል ምክር ቤት አሻፈረኝ ይበል:: ነገሩ ተዘጋ ማለት ነው:: የቀረት ወይ ህገ መንግሥቱን መጣስና አዲሱን ፖሊሲ ከሥራ ላይ ማዋል::ወይ አርፈው መቀመጥና የዚህን ክልል መልካም ፈቃድ መጠበቅ:: ያለጥርጥር የሚቀናቸው ህግ የመጣሱ ሂደት ነው:: ይህ ደግሞ የህግ የበላይነትን የጣሰ አደገኛ አሠራር ይሆናል:: አዲሱን ፖሊሲ የሚቃወሙት ኃይሎች ደግሞ ከቤኒሻንጉል ክልል ሰፋ ሊሉ ስለሚችሉ እንዲያውም አናሳው ኢህአዴግ በዚህ°ህገ ወጥ°ዘዴ ፕሮግራሙ ሲጣስ ሲያይ ዝም አይልም:: ለሌላ የትርምስ ወቅት በሩ ተከፈተ ማለት ነው::

35/ <u>በዚህ ህገ መንግሥት ሥር ምርጫ አሸንፍ የት ለመድረስ</u>?

ኢህአዴግና የሃገራችን ዲሞክራቶች ስለ መልቲ ፓርቲ ሥርዓት አንድ ዓይነት አስተሳሰብ እንደሌላቸው ግልጽ ነው:: እነመለስ ሃሳቡን የውጭ አሳዳሪዎቻቸውን ለመደለል ተቀበሉት እንጂ አያምኑበትም:: አይሰሩበትም:: አይፈልጉትም:: ጥያቄውን <u>በብዙ ፓርቲዎች መኖር</u> ብቻ ሊሸኙት ይፈልጋሉ:: ለና ግን ጥያቄው እስከዚህም እንደቻይና በክስ ዓይነት በአንድ ድርጅት አምሳል ተጠፍጥፈው የተሰሩ የዚያ ድርጅት ተለጣፊ የሆኑ መቶ ፓርቲዎች መኖራቸው አይደለም:: ቁም ነገሩ ልዩ ልዩ ፓርቲዎች መኖራቸውና ህልውናቸው በህግ መረጋገጡ ነው::

መልቲ ፓርቲ ስርዓት የልዩ ልዩ ፓርቲዎችን መኖር ይጠይቃል:: ማለትም የተለያዩ የፖለቲካና ርእዩተ ዓለም አመለካከት ያላቸው፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ፣ የሰሻልና የባህል ፖሊሲ ያላቸው:: እነዚህን ይዘው በህዝብ ፊት ለምርጫ የሚቀርቡ:: ሲያሸንፉ እነዚህን ፖሊሲዎች ከሥራ ላይ ለማዋል የሚደምሩ:: በሌላ አነጋገር ማጆሪቲ አግኝተው ከመጡ በኋላ የራሳቸውን ፖሊሲ እንጂ ተሸንፍ ከሥልጣን የወረደው ኃይል የቀየሰውን ፖሊሲ ከሥራ ላይ ለማዋል የማይገደዱበት ሁኔታ ያስፈልጋል:: በፈረንሳይና በእንግሊዝ ያየነው ነው:: ሶሻሊስቶች ሲያሸንፉ ባንኩን ትላልቅን ፍብሪካ ናሽናላይዝ ሲያደርጉ፣ ቀኞች ሲያሸንፉ ናሽናላይዝድ የሆነውን መልሰው ሲፈቱ:: በእንግሊዝ አገር ሌበር ወደ መንግሥት ያዘረውን ወይዘሮ ታቸር ወደ ግል ንብረትነት ሲመልሱት....ይኸ ሁሉ በተራ ምርጫ ማጆሪቲ አግኝተው ስለመጡ ወይም ማጆሪቲ አጥተው ከሥልጣን ስለወረዱ:: መልቲ ፓርቲዝም ይኸ ነው:: የኢህአዴግ ግን እንደዚህ አይደለም:: ነገ በተዓምር ተመርጠ

የመጣ ሌላ ኃይል ከፍ ብየ ባልኩት መሠረት በድፍን ኢትዮጵያ ከፍተኛ አብላጭነት አግኝቶ መአከላዊና የክልል ፖርላሜንቶች ካላጥለቀለቀ ወይም በህገወጥነት እሠራለሁ ብሉ የግጭትንና የኮንፍሮንቴሽን ጉዳና ካልመረጠ ከህዝቡ 90 ከመቶ ኑሮ የተንጠለጠለበትን የመሬት ጉዳይ በሚመለከት ለመከተል የሚገደደው የኢህአዴግን ፖሊሲ ነው:: የነገሩ አስደናቂነት እዚህ ላይ አያቆምም:: እርግጥ እንደሚባለው በሃቅ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚወክሉ ሰዎች በሙሉ ድምጽ ያጸደቁት ጨጨጨጨጨ ህገ መንግሥት በኖረን ኖሮ የመላው ህዝብ ፍላጎት ነው ተብሉ ለሱ መገዛት ይቻል ነበር:: በተጨባጭ የምናየው ግን የአንድ አናሳ ኃይልን ፖሊሲ ለመቀየር ህዝቡ ከዳር እስከዳር ተነስቶ በሙሉ ድምጽ ካልሆነ በስተቀር የማይቻል መሆኑን ነው::

ለዚህ ነው ስዚህ ህገ መንግሥት ሥር ምርጫ ተሳተፉ፣ በተቻለ ሁኔታው ለሃቀኛ ና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲመቻች እናደርጋለን የሚሉን ፈረንጆች አንድ ጥያቄ መመለስ ያለባቸው:: ምርጫ አሸንፈን የት ለመድረስ?? 06/02/95